INTERNATIONAL BACCALAUREATE
BACCALAURÉAT INTERNATIONAL
BACHILLERATO INTERNACIONAL

M01/166/S(1)

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIC A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 1**
**AMHARICO A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 1**

Thursday 17 May 2001 (afternoon)
Jeudi 17 mai 2001 (après-midi)
Jueves 17 de mayo de 2001 (tarde)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only. It is not compulsory for you to respond directly to the guiding questions provided. However, you may use them if you wish.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- Ne pas ouvrir cette épreuve avant d'y être autorisé.
- Rédiger un commentaire sur un seul des passages. Le commentaire ne doit pas nécessairement répondre aux questions d'orientation fournies. Vous pouvez toutefois les utiliser si vous le désirez.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento. No es obligatorio responder directamente a las preguntas que se ofrecen a modo de guía. Sin embargo, puede usarlas si lo desea.

ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ(ሽ) አስተያየትህን(ሽን) ስጥ(ስጪ)

1(ሀ)

# አንቻቦ

የዘመዶቹ ደም መቃባት፣ ከአምባዉ ውልፍት እንዳይል ክለከለው እንጂ ትቷቸው ለመሔድ ካሰበ ቆይቷል ። የባህል ልማድ እስረኛ በመሆኑ ከሚጠላቸውና ከሚጠሉት ዘመዶቹ መራቅ አልቻለም ። ጋብቻዉን አልጠላም ። እርሱ የጠላው ፣ ያንገሸገሸው፣ የሚወዳትን ለማጣት የሚደረገው ፍልሚያና በልጃገረዶቹ ላይ የሚፈጽመው ጉጂ ባህል ነው ። ከእርሱ ቀደም ብለው ትዳር የያዙት ጓደኞቹ በዚህ ከጋብቻ በፊት በሚደረግ ፍልሚያ ( ዶንጋ ) ምክንያት እየተሸነፉ ፍቅረኞቻቸውን አጥተው አንዳንዶቹ ነሆለል ሲሆኑ ፣ ሌሎቹ ደግሞ በአካባቢያቸው ተንቀው ፣ ተዋርደው የቢጤዎቻቸው መሣቂያና መሣለቂያ መሆናቸውን ያውቃል ። ስለዚህ፣አንቻቦ ለጋብቻ ሲባል የሚደረገውን ድብድብ ( ዶንጋ ) አይወደውም ። ገና ትርምስና ሲጀምር ነበር የጋብቻ ተራ ሲደርሰው፣ ይህንን ጥሪ እንደማይቀበለው በሕሊናው የወሰነው ።

እንኳንስ ዛሬ የመሠረተ ትምህርት ተምሮ ይቅርና ጥንትም ቢሆን አንቻቦ ከቤተ ዘመዶቹ ዐልፎ ከጐሣው የተለየ ባሕሪ ያለው ነበር ። የአንቻቦ ባሕሪ እንደ ብዙዎቹ የሙርሲ ጐሣዎች ገራምነትና ደግነት ያልተለየው ነው ። በራሱ አሳብ የመጥናት፣የመወሰንና በሌላው አሳብ ያለመገዛት ባሕሪ አለው ። ይህ ባሕሪው ከሌሎቹ የሙርሲ ጐሣዎች ይለየዋል ። ስለዚህ አንቻቦ በዚህ ባሕሪዉ ለእናቱም ሆነ ለአባቱ ቀርቶ ለጐሳው የሚመች ባለመሆኑ የልማድ ጠንቅ ይሆናል ብለው ሽንጐ እንዳይሰማ ፣ ንብ እንዳያረባ ፣ ገበጣ እንዳይጫወት፣ጠመንጃ እንዳያነግት ጐሳዉ መክሮ ወስኖበታል ።

በዚህ ምክንያት አንቻቦን ገበጣ ለመጫወት የሚጠይቀው ፥ ቀፎ ለመስቀል የሚያማክረው ፥ ጠመንጃ እናንግት ብሎ የሚያጐዳኘው ፥ ሸንጐ ለመስማት ‘እንሒድ’ የሚለው ጓደኛ የለውም ። እሱ እንኳ ፈልጐ ‘ገበጣ እንጫወት ፥ ቀፎ እንስቀል ፥ ሸንጐ እንሒድ’ ቢል አሳቡን አይቀበሉትም ። ካንዴም ሁለት ሦስት ጊዜ ሞክሮ ሳይሳካለት በመቅረቱ ዐድማ እንደ ተመታበት ገብቶታል ። ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ አንቻቦ የልብ ልብ የተሰማው ። የሚያስበው ፥ የሚወስነውና በተግባር ላይ የሚያውለው፥ እያንዳንዱ የድርጊት እርምጃ የእርሱን ማንነት ገልጾ ፥ በዚህ ባሕሪዉ የሚጠሉትንና ከኅብረተሰቡ ያገለሉትን የኋላ ቀር ልማድ እስረኞችንም አርነት ማውጣት እንደ ሚገባው ለራሱ ቃል ገባ ።

አንቻቦ ፥ ልቡ እንደ ድንጋይ እንዲጠጥር ፥ መንፈሱ እንደ በርኖስ እንዲኮሰኩስ ፥ አንደበቱ እንደ ተርብ እንዲናደፍ ያደረጉትን ሦስት ምክንያቶች ሲያስብ ይዘገንነዋል ። ቢሆንም በዚህ ምክንያት ሊደርስበት የሚችለውን ማንኛውንም ተጽዕኖ ያለ ቅሬታ ለመቀበል ዝግጁ ሆኗል ። ስለ ጠሉት ጠልቷቸዋል ። አንቅሮ ተፍቷቸዋል ። ስላኮረፉት አኩርፏቸዋል ። ብቸኝነት ሆኗል ጓደኛው ።

ተስፋዬ ብርሀኑ፥ <u>እነሆ</u>፥ ንግድ ማተሚያ ቤት፥ 1980

በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙት ዋና ዋና ጭብጦች /መልዕክቶች/ ምንድናቸው?
በጽሁፉ ውስጥ ዶንጋ እንደምን ቀርቧል?
አንቻቦ ምን አይነት ገፀ ባህሪ ነው? የአንቻቦ አመለካከት ለአንባቢው የቀረበበትን መንገድ አስረዳ/ጂ።

1(ለ)

የወሎዬው — የዲጋጉ
የትግሬው — ያክሱም ጥጉ
ላንቃው — እንደ ጎመን ዘር አረረ
ትንፋሹ — እንደ ሸክላ ተሰበረ
አንጀቱ — እንዳረግ ተሳሰረ
ዋ!... በየጥሻው — በያረንቋው — ወድቆ ቀረ

እስቲ ይታይሽ — ፀሐይቱ
አኗኗሩ... አሟሟቱ
ጭለማ አረግሽው — ሕይወቱን
የዚያን ወገኔን — እኔነቱን ፤
የማይ ጠብታ — ነስተሽ
የእህል ሽታ — ሰውረሽ
እሱን ቀቅለሽ
እሱን አንፍረሽ
ለበይ ሰጠሽው — ለጥንባንሳ ፤
ለጅብ መንጋ — ለሳቢሳ ።

ቀኑን ሙሉ ፣ ሌቱን ሁሉ ፤
ይህ ሆነና ፣ ካንቺ ውሉ...

አበራ ለማ፥ <u>የማለዳ ስንቅ</u>፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፥ 1980።

የገጣሚው የቃላት ምርጫና ምስል የመፍጠር ችሎታ በሚመለከት አስተያየት ስጥ/ጪ/።
ገጣሚው ስለፀሐይ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?
በግጥሙ ውስጥ ፀሐይ እንደምን ተገልጻለች?